Amharic



# የበጋ ጊዜ ንባብ
# (ትምህርት ቤት ሲዘጋ)

## ልጅዎ በትምህርቱ እንዲሳካለት ይርዱት፡

በበጋ/ሳመር ጊዜ የሚያነቡ ልጆች በትምህርታቸው ውጤታማ እንደሚሆኑ ያውቃሉን?

ልጅዎ በንባብ እንዲጎበዝ የሚረዱባቸው መንገዶች፡

- ልጅዎ የንባብ ቤት መታወቅያ/ካርድ ከአካባቢው ሕዝባዊ፡ ንባብ ቤት ያውጡለት፡
- ልጅዎ በበጋው የንባብ ጊዜ እንዲሳተፍ በንባብ ቤቱ የነፃ የበጋ የንባብ ፕሮግራም ከበብ ያስመዝግቡት፡
- ልጅዎ በየቀኑ እንድያነብ ያነቃቁት፡ ልጆች በበጋ ጊዜ ካነበቡ ትምህርት ቤት ሲከፈት በትምህርታቸው ውጤታማ ይሆናሉ።
- ልጆችዎ የሚወዱትን መጽሓፍ እንዲመርጡ ዕድል ይስጧቸው። ልጆች በደስታ ካነበቡ ብዙ ማንበብ ይችላሉ፤ ችሎታቸውም ይሻሻላል።
- ልጆችዎን ስለሚያነቧቸው መጽሓፍት ይጠይቋቸው። በራሳቸው ቃላት ስለሚያነቡት መጽሓፍ ሲገልጹ፤ በበለጠ ስለሚያነቡት ታሪክ ይገባቿል።
- ለልጅዎ መጽሓፍ ያንብቡለት፡ ወይም በድምጽ የተቀረጸውን መጽሓፍ አብረው ያዳምጡ። ስለተካፈላችሁት ታሪክ ጉዳይ መነጋገሩ ልጅዎ አዳዲስ ቃላትና አዳዲስ ሃሳቦችን እንዲያውቅ ይረዷል።
- እርስዎም ለልጆችዎ ማንበብ እንደሚወዱ ያሳዩ። በግልዎ በምርጫዎ በሆነ ቋንቋ የተዘጋጀ መጽሓፍ ያንብቡ።